

COVID-19 CRISIS

# Sesame Sector

## Introductory brief for stakeholders

*Woman cleaning sesame seeds. Photo: Flo Dirks*

## ፈጣን የሰሊጥ ዘርፍ ዳሰሳ/ቅኝት፡ ለሰሊጥ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት የተዘጋጀ አጭር ገለጻ

### የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ19) ወረርሽኝ በግብርና ዘርፉላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ

የኮቪድ19 ወረርሽኝ እና ወረርሽኙን ለመከላከል እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እያስከተሉ ይገኛሉ፡፡ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ለግብርናው ዘርፍ የተለየ ትኩረት በመስጠት እና ተጨባጭ እርምጃዎችን በመውሰድ የአርሶ አደሮችን ገቢ፣ የስራ እድል እና የምግብ ዋስትና መታደግ ይገባል:: የዓለም ባንክ አፍሪካ ለተከታታይ 25 ዓመታት እያስመዘገበች ያለችው ምጣኔ ሃብታዊ እድገት በ2012 እንደሚቀንስ ትንበያውን አስቀምጧል:: የግብርናው ዘርፍ በወረርሽኙ ክፉኛ ይጎዳሉ ተብለው ከተፈረጁ የምጣኔ ሃብት ዘርፎች መካካል ቀደሚ ነው:: የሀገር ውስጥ ምርት መቀነስ፣ ከውጭ የሚገቡ የምግብ ሸቀጦች ማነስ እና የምግብ ዋስትና አለመኖር የሚጠበቁ ተግዳሮቶች ናቸው:: በአለም አቀፍ ደረጃ የምግብ ዋስትና ኮሚቴ አባል ሆነው የሚሰሩ ከፍተኛ ምሁራን እንደጠቆሙት ወረርሽኙ በሀገር ውስጥ እንዲሁም በአለም አቀፍ የምግብ ሸቀጥ ገበያዎች ላይ አለመረጋጋት እንዲኖርና በዚህም ምክንያት የምግብ አቅርቦት እጥረት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

ከወቅቱ ወረርሽኝ አንጻር የቀጣዩ ምርት ዘመን የሰብል ልማት እና ግብይት እንቅስቃሴ በተቻለ መጠን ውጤታማ እንዲሆን መስራት ያስፈልጋል:: ይህንንም ለማከናወን ወረርሽኙን ለመከላከል በመንግስት የተላለፉ ውሳኔዎች በግብርናው ዘርፍ ላይ እያደረሱ ያሉት ተጽዕኖ በአግባቡ መለየት እና በአርሶ አደሮች ምርት እና ገቢ ላይ የሚያደርሱትን ጫና ሊቀንሱ የሚችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል:: ይህ አጭር መግለጫ የሰሊጥ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት በጋራ የሰሊጥ ልማት ቀጠናዎችን በመዳሰስ ለተለዩ ችግሮች የመፍትሔ አማራጮችን መለየት የሚቻልባቸውን የአሰራር መንገዶች የሚጠቁም ነው::

### የሰሊጥ ዘርፉ ለክልሉ ብሎም ለሀገሪቱ እያስገኘ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ አደጋ ውስጥ ነው

እንደሚታወቀው የሰሊጥ ልማት ወቅታዊ እና ከወቅት ጋር ከሚፈጠር የአየር ጸባይ ጋር የተሳሰረ ነው:: የሰሊጥ ልማት በአነስተኛና በባለሃብት አርሶ አደሮች ማሳ የሚለማ እና ብዙ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ የግብርና ዘርፍ ነው:: ይህ ወሳኝ የግብርና ዘርፍ አሁን ላይ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በተለያየ መልኩ ጥላውን አጥልቶበት ይገኛል:: ለምሳሌ...

- አርሶ አደሮች የሚፈልጉትን ግብዓት፣ ብድር፣ የቀን ሰራተኛና የመሳሰሉትን በወቅቱ ማግኘት ካልቻሉ ምርታማነታቸው ይቀንሳል::
- በትራንስፖርት ስምሪት ላይ የተጣለው ገደብ በዚሁ ከቀጠለ የቀን ሰራተኞች መንቀሳቀስ ስለማይችሉ ገቢ አያገኙም::
- የቀን ሰራተኞች ወረርሽኙን ለመከላከል የሚመከሩ የጤና ተግባራትን ማክበር እና መተግበር ካልቻሉ በሽታውን ሊያሰራጩ ይችላሉ::
- ሰሊጥን ወደ ውጭ መላክ የማይቻል ከሆነ የሰሊጥ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል:: ከዘርፉ የሚገኘው ገቢም በከፍተኛ ሁኔታ ይጎዳል::
- የምግብ ሸቀጮች በአንንድ ቦታዎች የሚከዘኑ ከሆነ፣ የመጓጓዣ ችግር ካለ እና የአርሶአደሮች ገቢ የሚቀንስ ከሆነ ብዙ የአርሶአደር ቤተሰቦች የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት እጥረት ይገጥማቸዋል::

ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት የግብርና እሴት ሰንሰለቶች እንዴት ሊስተጓጎሉ እንደሚችሉ ያሳያሉ፡፡ ሆኖም ግን ችግሮችን ቀድሞ መረዳት፣ በፍጥነት የመፍትሔ እርምጃዎችን ለማስቀመጥ እና ስጋቶችን ለመቀነስ ይረዳል፣ ምርት እና ገቢንም ለማሳደግ ያስችላል::

### የሰሊጥ ዘርፍ ፈጣን ዳሰሳ

የዳሰሳ/ቅኝቱ ጥናቱ ሶስት ዓላማዎች አሉት፣ 1) ወረርሽኙ ሊያስከትል በሚችለው ጉዳት ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ መፍጠር 2) ወረርሽኙ በየትኛው ዘርፍ ከፍተኛ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል በመተንበይ ለመንግስት ውሳኔ ሰጪ አካላት፣ ለኢንድስትሪዎች፣ ለምርምር ተቋሟት እና ለሲቪክ ማህበራት መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ የማስጠንቀቂያ/የማንቂያ ሰነዶችን ማዘጋጀት3) በተለዩ ችግሮች ዙሪያ የመፍትሔ ሃሳቦችን በማስቀመጥ በእቅድ ለመተግበር ያግዛል:: በተጨማሪም አጋር አካላት ለዳሰሳው የሚረዳውን ቅፅ በሌሎች ዘርፎች ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርጉ ይችላሉ::

### ትኩረት በወሳኝ ተግባራት ላይ

የዚህ ፈጣን የዳሰሳ ስልት በሁሉም የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ለሚከተሉት አስር ተግባራት ትኩረት ይሰጣል:: እነርሱም፣(i) የሰሊጥ ልማት (ii) የሰሊጥ ስነ-ምህዳር (iii) በሰሊጥ ዘርፍ የተሰማራውን ማህበረሰብ (iv) በሰሊጥ ዘርፍ ያሉ/የተሰማሩ ማህበራትና ድርጅቶችን (v) የሰሊጥ እሴት ሰንሰለት (vi) ከሰሊጥ ጋር የተገናኘ አገልግሎት (vii) አጠቃቀም (viii) የሰሊጥ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት ትብብር (ix) ሰሊጥን የተመለከቱ ፖሊሲዎች እና ህጎች (x) ከሰሊጥ የሚገኝ ገቢ እና ለሰሊጥ ልማት የሚደረግ ኢንቨስትመንት ናቸው፡፡ የአሰራር ስልቱ ሁሉን አቀፍ የሆነ ዳሰሳ በማድረግ እና በይበልጥ የተጎዱ ዘርፎችን በመለየት በአፋጣኝ መወሰድ ያለበትን እርምጃ ለመጠቀም ይረዳል::

---

*1] World Bank, 2020. An Analysis of Issues Shaping Africa's Economic Future. Africa's Pulse, No. 21, Spring 2020. World Bank, Washington, DC (link). 2] HLPE, 2020. Interim Issues Paper on the Impact of COVID-19 on Food Security and Nutrition. HLPE Secretariat, Rome (link).*

## የአተገባበር ስልት/ዘዴ

የዳሰሳ ጥናቱ በየጊዜው የሚከናወን ሲሆን በሰሊጥ ዘርፉ በተለያየ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያሳትፋል:: የኤክስፐርቶች ቡድን በያሉበት ሆነው ፈጣን የቅኝት ጥናት ያደርጋሉ፡፡ ከቅኝት ጥናቱ የሚገኘው ውጤት በቡድንጥልቅ ውይይት ይደረግበታል::

የመጀመሪያ ተግባር ከመንግስት ተቋሚት፣ ምርምር፣ ኢንደስትሪ፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋሚት፣ የአርሶአደር ማህበራት እና ከአርሶአደሮች የተውጣጣ አጥኝ ቡድን /ፓነል/ ይቋቋማል:: የቡድኑ አባላት ለ15 ደቂቃ የተዘጋጁ መጠይቆችን በመመለስ በኢንተርኔት በሚደረገው የቅኝት ጥናት ይሳተፋሉ:: በቅኝት ጥናቱ የተካተቱ ጥያቄዎች ከግብዓት ጀምሮ ያሉ ሁሉንም ተግባራት የሚያጠቃልሉ ሲሆን፣ በጥናቱ ወቅት የሚተገበሩ ስራዎች ትኩረት ይደረግባቸዋል:: ከዚህ ቅኝት ጥናት የተገኙ መልሶች ተጠቃለው ለቡድን ውይይቱ ግብዓት ይሆናሉ:: የቡድን ውይይቱ አባላት ከ5 እስከ 8 የሚሆኑ ሲሆን በኢንተርኔት በሚካሄደው ውይይት የቅኝት ጥናቱን ውጤት ይገመግማሉ፤ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎችን እና ባለድርሻ አካላትን ይለያሉ::

የቅኝት ጥናቱ እና የቡድን ውይይት ውጤት ተጠቃሎ ለቅድመ ጥንቃቄ ማንቂያ/ማስጠንቀቂያ ይሆናል:: ይህ የማስጠንቀቂያ ሰነድ በዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ችግርን በመለየት፤ አስፈላጊውን የመፍትሔ እርምጃ በመጠቆም፤ ባለድርሻ አካላት ሃለፊነትን እንዲወስዱ እና እንዲተገብሩ የሚረዳ ነው:: የማስጠንቀቂያ ሰነዱ የተለያዩ የማህበራዊ የትስስር ድረ-ገጾች፣ ብሎጎች፣ በምስል ወድምጽ እና ሌሎች የተለያዩ የተግባቦት መንገዶችን በመጠቀም ለሚመለከታቸው አካላት ይላካል::

የመጀመሪያውን የማንቂያ ሰነድ በሰኔ ወር 2012 ዓ.ም የመጀመሪያ ሳምንት ለማዘጋጀት ታቅዷል:: በቀጣይ በተመሳሳይ መንገድ በየወሩ ሰነዱን ለማዘጋጀት የታሰበ ሲሆን፣ ይህም ማለት ቀጣዩ ሰነድ ሐምሌ ላይ ይዘጋጃል፡፡ ከሁለቱ ወራት በኋላ የአሰራር ስልቱ ውጤታማነት ይገመገማል፡፡

## ትብብር/ፓርትነርሽፕ

በርካታ የሰሊጥ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትን ፈጣን የዳሰሳ ቅኝት የሚያስተባብረው የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ የድጋፍ ፕሮግራም (ቤኔፊት-ኤስ ቢ ኤን) ከግብርና ሚንስቴር፣ ከአማራና ትግራይ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ነው፡፡ ቤኔፊት-ኤስ ቢ ኤን በቤኔፊት ፓርትነርሽፕ ውስጥ ከሚገኙ ፕሮግራሞች አንዱ ነው፡፡ ለዚህ ፓርትነርሽፕ የፋይናንስ ድጋፍ የሚያደርገው የደች የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አዲስ አበባ በሚገኘው የኒዘርላንድስ ኢምባሲ በኩል ነው፡፡ የሰሊጥ መረብ የድጋፍ ፕሮግራም ዋና አላማ ተፎካካሪ፣ ቀጣይነት ያለው እና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት አሳታፊ የሆነ የሰሊጥ ልማት በማካሄድ የአርሶአደሮችን ገቢ ማሳደግ ነው፡፡ከሰሊጥ ባሻገር የፈረቃ ሰብሎችም ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ የድጋፍ ፕሮግራሙን በዋገኒንገን ዩኒቨርሲቲ የሴንተር ፎር ዲቨሎፕመንት ኢኖቬሽን ያስተባብረዋል፡፡

The ‘Rapid assessment of the Sesame Sector’ is published within a series of ‘Rapid assessments’ and ‘Alerts’ in multiple countries, and is a WCDI Sector Transformation publication.

Please cite as: Rapid assessment of the sesame sector. Introductory brief. Wageningen Centre for Development Innovation, 27 May 2020.

For more information:
Wageningen Centre for Development Innovation, The Netherlands
info.cdi@wur.nl | www.wur.eu/wcdi
**Project lead:** Flo Dirks
**Email:** flo.dirks@wur.nl

Sesame Business Network/BENEFIT
www.sbnethiopia.org
**Contact person:** Anteneh Mekuria Tesfaye
**Email:** anteneh.sbn@gmail.com